**መግለጫ**

# የሴት ልጆችን መግረዝ በመቃወም የወጣ

## ይህ መግለጫ ለምን አስፈለገ?

ይህን መግለጫ ወደ ውጭ ኣገር ይዘዉት መሄድ ይችላሉ። ቤተ ሰቦቻቸውንም ማሳየትም ይችላሉ። በዚሁ መሰረት የሴት ልጆች መግረዝ በሆላንድ በሕግ የሚያስቀጣ መሆኑን ሊያስረዱ ይችላሉ። ሴት ልጅዎን ካስገረዙ እርስዎ በወህኒቤት ሊገቡ እንደሚችሉ ያብራራሉ።

በየግዜው ወደ ውጭ ኣገር በሚሄዱበት ጊዜ ይህንን መግለጫ እንዳይረሱት ከጉዞ መስረጃዎችዎ (ከፓስፖርትዎ) ጋር ያስቀምጡ።

## ሴት ልጅን መግረዝ በሕግ ያስቀጣል።

**የሴት ልጅ ግረዘት በሰው ኣካል የሚፈጸም ከባድ በደል ስለሆነ በሕግ ያስቀጣል። ሴት ልጆችን መግረዝ የልጆችንና የሴቶችን ሰብኣዊ መብት መግፈፍ ነው። በሆላንድ ማነኛውም ዓይነት የሴቶች ግርዛት ብሕግ የተከለከለ ነው። ይህ ሕግ ለማነኛው በሆላንድ ኣገር የሚኖር ሰው፥ ቋሚ የመኖርያ ፍቃድ ባይኖረውም ይመለከትዋል።**

በሆላንድ የሴት ልጅ ግርዛት እንደ የልጅ በደል ተወስዶ ያስቀጣል። ይህ የግርዛት ወንጀል እስከ 12 ኣመት የሚደረስ እስራት ያስከትላል። የመግረዝ ወንጀሉ በወላጆች ከተደረገ ከፍ ያለ ቅጣት ያስከትላል (በሆላንድ መቅጫ ሕግ ኣንቀጽ 300 እስከ 304)

በልጆቻቸው ላይ የመግረዝ ተግባርን የፈፀሙ ወላጆች ፣ ድርጊቱን በሌላ ሃገር መፈፀማቸው ከተረጋገጠ፣ በኔዘርላንድ ህግ መሰረት ተገቢውን ቅጣት እንዲቀበሉ ይደረጋል።

ወላጆችም ሆኑ ሌላ ወገን በሴቶች ላይ የግርዘት ተግባር እንዲፈፀም ካደረጉት ወይም በሌላ ሃገር እንዲካሄድ ካቀናጁ፣ በኔዘርላንድ ህግ መሰረት ይቀጣሉ።[1]

ወላጆች ይህንን የግርዘት ድርጊት በልጃቸው ላይ መፈፀማቸው ተረጋግጦ የተፈረደባቸው ከሆኑና ወይም በሌላ አካል እንዲፈፀም ካደረጉት፣ የሆላንድ ፓስፖርት ከሌላቸው በኔዘርላንድ ውስጥ መኖሪያ ፈቃድ የማግገኘት መብታቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

## ሴት ልጆችን መግረዝ በጣም ጎጂ ልማድ ነው።

**ሴት ልጆችን መግረዝ በጤንነታቸው ላይ ከባድ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። በሚገረዙበት ግዜ፡ ብዙ ደም ሊፈሳቸው ይችላል። በዚህ ምክንያት ወደ ኣደገኛ በሽታ ወይም ሞት ሊዳረጉ ይችላሉ።**

ከተገረዙም በኋላም ብዙ ስቃይ ይደርስባቸዋል። ለምሣሌ፣ በሚሸኑበትና የወር ኣበባ የሚያዩበት ግዜ፡ , በእርግዝና በወሊድ ጊዜ ከባድ ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል። ከጊዜ በኋላም የመንፈስ ጭንቀት ልያመጣባቸው ይችላል።በእነዚህ ሁሉ ምክንያት ብዙ ሴቶች ብሂወታቸው ሙሉ ስቃይና የጤና ችግር ሊገጥማቸው ይችላል።

ይህ መግለጫ የሴት ልጅ ግርዛት በመቃወም የወጣ ሲሆን፣ ኣላማው ልጃገረዶች በኣካልዊና በኣእምሮኣዊ ጤነኛ ሆኖው እንድያድጉ ነው።

ከኣክብሮት ጋር,

Drs. M.J. van Rijn
የሃገሪቱ የጤና ጥበቃ፣ እርዳታና ስፖርት ሚኒስተር

Mr. I.W. Opstelten
የደህንነትና ፍትህ ሚኒስተር፡

## ጥያቄ ኣለዎት?

ስለ ሴት ልጅች ግርዛትና ስለዚህ መግለቻ ትጸግሚል? ጥያቄ ካለዎት፣ በማነኛውም ጊዜ ወደ ሚመለከተው ኣማካሪ ጽህፈት ቤት ወይም ወደ ማዛጋጃ ቤቶች ጤና (CGD) ኣገልግሎት በመሄድ ከሃኪም ወይም ከነርስ ጋር ቀጥሮ መያዝ ይችላሉ። ለተጨማሪ ማስረጃ፣ በዚህ ድህረ ገጾች እንግሊዘኛ ቋንቋ መጎብኘት ይችላሉ።
**www.meisjesbesnijdenis.nl** እና **www.tegenvrouwenbesnijdenis.nl**

ይህ መግለጫ የወጣው ፤

በጤና ጥበቃና ስፖርት ሚኒስቴርና

በደህንነትና የፍትህ ሚኒስቴር ነው::

መጋቢት 2006 ዓ. ም::

Amhaars

# የሴት ልጆችን መግረዝ በመቃወም የወጣ መግለጫ

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ድርጅቶች የተደገፈ ነው፣

dhr. drs. A. Koster
ኣክቲዝ የጤና ጥበቃ ኣቅራቢዎች ማሕበር

mw. L.J. Smit
የዳች የህክምና የወጣቶች ጤና ጥበቃ ማህበር

dhr. A. Ware
የሶማል ፌደራስዮን ማህበር በሆላንድ

mw. G. Bouman
የሆላንድ የወጣቶች ጥበቃ ተወካይ

dr. J. Wijma
የዳች የማህጸን ባለሞያዎች ህብረተሰብ

mw. drs. M. T. M. van Berkum
ፋሮስ፣ የሆላንድ የዕውቀትና የምክር ማህል ለስደተኞችና ጤንነት

dhr. H.A.M. Backx
የዳች የመዘጋጃቤት የጤና ኣገልግሎት ማህበር በሆላንድ

prof. dr. R.J. van der Gaag
የዳች የንጉሳዊ ቤተሰብ የህክምና ማህበር

mw. L. Rentes
የሆላንድ የንጉሳዊ ቤተሰብ **Midwives** ድርጅት

mw. H. Zijlstra
የሆላንድ የነርሶች ህብረት

mw. drs. F. Z. Özgümüş
የስደተኞች ድርጅት በሆላንድ

የዎላጆች ፊርማ

የሴት ልጆችን መግረዝ በመቃወም የወጣ መግለጫ